የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጉምሩክ ኮሚሽን
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
CUSTOMS COMMISSION

ቁጥር/ Ref.No. 4/047815
ቀን/Date ሚያዝያ 27 2015

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ
በያሉበት

ጉዳዩ፦ ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 519/2014 ይመለከታል፤

ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 519/2014 ተግባራዊ እንዲሆን በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ወጥቷል።

ስለሆነም ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 519/2014 ተግባራዊ እንዲደረግ 4 ገጽ ተያይዞ የተላከ መሆኑን አሳስባለሁ።

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ግልባጭ፦

- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ
- ለተቋማዊ አቅም ድጋፍ ዘርፍ
- ለየታሪፍ ምደባና ሥሪት አገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት
- ለዋጋ ትመናና ልማት ዳይሬክቶሬት
- የገቢ ዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት
- የትራንዚትና መጋዘን አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
- የጉምሩክ አቤቱታ አጣሪ ዳይሬክቶሬት
- የጉምሩክ ስራ አመራር ሥርዓት ፕ/ጽ/ቤት
- የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ዳይሬክተር
- ለጉምሩክ ኮምንኬሽን ስራ ሂደት

ጉምሩክ ኮሚሽን፣



ስልክ/Tel:- +251 116 67 54 58
:- +251 116 62 98 19
ፖ.ሳ.ቁ. 2559
Email: hocrecordopr@gmail.com
Website:- www.ecc.gov.et
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአሶሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሀዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሠመራ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት
- ለታጁራ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት

<u>**ባያሉበት**</u>፤

7

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

28th Year No. 48
ADDIS ABABA, 22nd August, 2022

**ማውጫ**

ደንብ ቁጥር ፭፻፲፱/፳፻፲፬
ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ ደንብ...............ገጽ ፲፬ሺ፬፻፳

**Content**

Regulation No. 519/2022
Social Welfare Levy on Imported Goods Regulation ........................................Page 14420

## ደንብ ቁጥር ፭፻፲፱/፳፻፲፬

## ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

ለትምህርት፣ ለሥልጠና እና ለጤና ተቋማት መልሶ ማቋቋሚያ እና ግንባታ እንዲሁም ለሌሎችም የማህበራዊ አገልግሎቶች ማስፋፊያ የሚውል ተጨማሪ ገቢ መሰብሰብ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዓለም አቀፍ የተዋሃደ የሸቀጦች አሰያየም እና አመዳደብ ስርዓት ማፀደቂያ አዋጅ ቁጥር ፷፯/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፬ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ለማስከፈል የወጣ ደንብ ቁጥር ፭፻፲፱/፳፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## REGULATION No. 519/2022

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR SOCIAL WELFARE LEVY ON IMPORTED GOODS

WHEREAS, it has become necessary to collect additional revenue earmarked for the rehabilitation and construction of education, training and medical facilities and expansion of other social services;

NOW, THEREFORE, this Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 4 of the International Convention on the Harmonized Commodity Description and Coding System Ratification Proclamation No. 67/1993.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Social Welfare Levy on Imported Goods Regulation No.519/2022."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 53:00

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation

፪. <u>የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ስለማስከፈል</u>

በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ ከቀረጡ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር በጉምሩክ ታሪፍ ደንብ የተዘረዘሩ ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ በዚህ ደንብ መሠረት የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ይከፈልባቸዋል፡፡

፫. <u>የማህበራዊ ልማት ቀረጥ የሚውልበት ተግባር</u>

፩/ በዚህ ደንብ መሠረት የሚሰበሰበው የማህበራዊ ልማት ቀረጥ መንግሥት የትምህርት፤ የሥልጠና፣ የጤና እና ሌሎችንም የማህበራዊ መሠረተ ልማቶች ለማቅረብ እና ወጪያቸውን ለመሸፈን ለሚያከናውነው ተግባር የሚውል ይሆናል፡፡

፪/ ከማህበራዊ ልማት ቀረጥ የሚሰበሰበው ገቢ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያፀድቀው በጀት መሠረት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ለተዘረዘሩት ተግባራት ይውላል፡፡

፬. <u>የማስከፈያ መጣኔ</u>

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ በዚህ ደንብ በተመለከተው መሠረት ፫ ፐርሰንት የማህበራዊ ልማት ቀረጥ እየተጣለ ይሰበሰባል፡፡

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰበው የማህበራዊ ልማት ቀረጥ በሌሎች ሕጎች መሠረት ከሚሰበሰበው ቀረጥ እና ታክስ በተጨማሪ ይሆናል፡፡

2. <u>Imposition of Social Welfare Levy</u>

There shall be levied, in accordance with the provisions of this Regulation, a social welfare levy on all goods imported into Ethiopia specified in the Customs Tariffs except those exempted under Article 6 of this Regulation.

3. <u>Purposes of the Social Welfare Levy</u>

1/ The Social Welfare Levy collected in accordance with this Regulation shall be used to fulfill the commitment of the Government to provide and finance education, training, health and other social services.

2/ The Social Welfare Levy shall be used for purposes specified under Sub-Article (1) of this Article in accordance with the budget appropriation to be made by the House of Peoples' Representatives.

4. <u>Rate of Social Welfare Levy</u>

1/ Subject to Article 6 of this Regulation, Social Welfare Levy of 3 percent shall be levied and collected on goods imported in accordance with this Regulation.

2/ The Social Welfare Levy levied on imported goods under this Regulation is in addition to any other customs duties and taxes collected under applicable laws.

Ethiopian Customs Commission Records & Documentation

**፭. የስሌቱ መሠረት**

፩/ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ስሌት መሠረት የዕቃው ዋጋ፣ ኢንሹራንስ እና የማጓጓዣ ወጪ ድምር ይሆናል፡፡

፪/ የማህበራዊ ልማት ቀረጥ ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ለሚከፈሉ ሌሎች ቀረጥ እና ታክሶች መሠረት አይሆንም፡፡

**፮. ከማህበራዊ ልማት ቀረጥ ነፃ ስለመሆን**

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ከማህበራዊ ልማት ቀረጥ ነፃ ናቸው፡-

፩/ የዲፕሎማቲክ ልዩ መብት ያላቸው ሰዎች እና ድርጅቶች፣

፪/ ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ስለተጣለ ተጨማሪ ቀረጥ በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፫/፲፱፻፺፱ መሠረት ተጨማሪ ቀረጥ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች፣ እና

፫/ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በገንዘብ ሚኒስቴር በሚወጣ መመሪያ ከታክሱ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች፡፡

**፯. የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት**

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፮ (እንደተሻሻለ) እና አዋጁን መሠረት በማድረግ በወጡ ደንቦች የተመለከቱ ድንጋጌዎች ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን የማህበራዊ ልማት ቀረጥ በማስላት፣ በመሰብሰብ እና በወንጀል ተጠያቂነት ረገድ አግባብነት እስካላቸው ድረስ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

**5. Basis of Computation**

1/ The basis of computation for the Social Welfare Levy levied under this Regulation shall be the aggregate of cost, insurance and freight (CIF) value.

2/ The Social Welfare Levy shall not serve as a base for any other tax imposed on imported goods.

**6. Exemption from the Social Welfare Levy**

The following shall be exempted from the Social Welfare Levy:

1/ persons and organizations with diplomatic privileges;

2/ goods that are subject to the sur-tax levied under Import Sur-Tax Council of Ministers Regulation No. 133/2007; and

3/ goods exempt by a Directive to be issued by the Ministry of Finance due to social and economic reasons.

**7. Applicability of Laws**

The provisions of the Customs Proclamation No. 859/2014 (as amended) and Regulations issued thereunder shall apply in relation to the Social Welfare Levy calculation and collection on imported goods and criminal liability, as the case may be.

Ethiopian Customs Commission Records & Documentation

፰. <u>ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን</u>

ይህ ደንብ ከሐምሌ ፴ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፬ ዓ.ም

ዐብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

8. <u>Effective Date</u>

This Regulation shall enter into force as of the 6th Day of August, 2022.

**Done at Addis Ababa, on this 22nd Day of August, 2022.**

ABIY AHMED (DR.)
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት

Ethiopian Customs Commission
Records & Documentation
No.2